# ፀጥታ

ማለዳ ላይ ፀሐይ ስትወጣ ታምራለች። በሙሉው ቀን ውስጥ ሊታይ የማይችለውን ውበትና መረጋጋት ለምታርፍባቸው ዛፎችም ትሠጣለች። እኛ ሁላችንም ያንን ዓይነት ፀጥታ እንፈልጋለን። ፀጥ ያለ ሰላም። ምናልባት ዐይናችንን ዘግቶ የመከፈት ያህል ፀጥታም ቢሆን ፀጥታን እንፈልጋለን።

ለአንዲት ሰከንድም ቢሆን ስለአንድ ነገር አለማሰብና አለመጨነቅ ደስ ይላል። አዎ ... ስለ አንድ ስለማንፈልገው አሊያም ስሌለንን ነገር ማሰብ መጨነቅ አንፈልግም። እዚያ መሆንን መፈለግ ደስ የሚል ነገር ነው። በፀጥታና ሰላም ውስጥ። በመረጋጋት ውስጥ። ምናልባትም በዚህ ቀን ውስጥ ደስ የሚለው ጊዜ ይህ ነው። ደስ የሚል ፀጥታ!።

ይህ ቀን የተለየ ነው ብሎ ለማሰብም ተስፋ ነው።



CamScanner

# ከመሞትህ በፊት ሙት

አምላኬ ሆይ!

ልጠፋና መንገድ ልስት እንደምችል ንገረኝ፤

አንተው ባለህበት ራሴን ላጣ እንደምችል ንገረኝ፤

በእውነተኛው መመራት መሃል በማደርገው ትግልና ጥረት

እስከዘላለሙ ተሰብሬ ልቀር እንደምችል ንገረኝ።

እናም ...

ባንተ ውስጥ

ላንተ ስል

ካንተ ጋር

እስከዘላለሙ እዚሁ እንደምቀር ንገረኝ

እዚሁ እያለሁ የራቅኩ መሆኔን ንገረኝ፤

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) "ከመሞትህ በፊት ሙት።" አላሉም ወይ?

ስለነኚህ ቃላቶች ሳስብ ... መጀመርያ ላይ ዝምብሎ ለማስታወስ ያህል የተናገሩት ቃል ይመስለኝ ነበር።

ካንተ ጋር መገናኘታችን እንደማይቀር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ያስተላለፉት መልዕክት መስሎኝ ነበር።

ግና ከመሞቴ በፊት እንዴት ልሞት እንደምችል አሰብኩ፤

ሰውነቴ እዚሁ እያለ ከዚህ ዓለም የወጣች ነፍስ እንዴት ሊኖረኝ እንደሚችል አሰላሰልኩ፤

እግር በጎዳና ላይ ቢራመድም ከዱንያ ትብታብ የወጣች ልብ፤

ቅርፊቷ እዚሁ እያለ ሙሉ እረፍትና እርካታን ከአምላኳ ጋር የምታጣጥም ነፍስ፤

እዚያ ሳትደርስ በፊት ቀድማ እዚያ የምትደርስ ነፍስ፤

ተገንጥላ በርራ የሄደች ነፍስ፤



CamScanner

እጅግ እውነት እጅግ ጥልቀት እና እጅግ ትከከለኛ በሆነ መልኩ የረጋችና የተረጋጋች ነፍስ፤

ኣሷ ናት ከመሞቷ በፊት የሞተች፤

ከእውነተኛው ሞት በፊት ሞትን ቀድማ የገደለች፤

አንድ ታላቅ ዓሊም አላህ እንዲህ ይላሉ - "በዚህ ምድር ላይ ያለችውን ጀነት ያልገባ፤ የሚቀጥለውን ዓለም ጀነትም አይገባም።"

## አድነኝ

ደግነትህን እንጂ ተስፋ የምጥልበት ምንም ነገር አንደሌለኝ አውቃለሁ። የተሰበሩ ጉዳቶችን ይዤ ደጃፍህ ላይ ቆሜያለሁ። ያንተን በር መከፈትንም እጠብቃለሁ። ከዚህ ማዕበል አድነኝ። ከባሮችህ ሁሉ ረዳት የሌለኝ አቅመ ቢስ ነኝ። መንገድህን ለማግኘት ጥቅጥቅ ባለው ጫካ ውስጥ እባክናለሁ። ግና የጫካው ዛፎች ሁሉ ተመሳስለዉብኛል። እያንዳንዱ መንገድም ወደመነሻው ነው የሚመራው። እኔ ግራ ገብቶኛል። አንተ ካላዳንከው በስተቀር ከዚህ ጫካ ውስጥ መውጣት የሚችል ማንም የለም። አድነኝ። አድነኝ። ራሴን ማዳን የማልችል ደካማ ነኝና።



CamScanner

አስታውሰው ልብሀም ላይ ፃፈው

ከዚያ

ዓለም እንዲያነበው ስጣቸው

ልብሀ ከፍት መጽሐፍ ነው።